# መለስ ቀለስ አለ

ከጌትነት

እንደ አጼ ምኒልክ ልግዛችሁ እያለ
በአፅሙ ሲገዛ መለስ ቀለስ አለ

ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል
ጉልቻ ቢቀየር መች ወጥ ያጣፍጣል

ከች አለ ደኪሴ ሊያነባ ለመለስ
ከነውጢስቢሩ ተጠናግሮ ሊያለቅስ

እንዲህ ነው መገልበጥ ሐረግ መለቃቀም
ምን ያስደንቀናል ፓሮት ቃል ቢደግም

ስማን በፓርላማ ሲያቅራራ ሲያጓራ
እየደጋገመ ጌታውን ሲጠራ

ላያዛልቅ ጸሎት
ትርፉ ጣር ለማብዛት
ለውግዘት ለቅስፈት

ራሱን ያልቻለ የገደል ማሚቶ
ኮፒ ሙታነ መንፈሱን አዘጋጅቶ

አሸለበ እስከወዲያኛው
ላይመለስ መርዘኛው

ሙት አይወቀስ
ንጉስ አይከሰስ

ሲባል የነበረው
መናገር መብት ነው

መውቀስም እንዲሁ
የፖለቲካ ሀሁ

ወጡ ሳይወጠውጥ
ወስከምባው ቅጥጥ
ጋሼ ደኪሴ ባለ መነጢሩ
ወዴት ነው ሰፈሩ

ርምጃና ሩጫ እየቀላቀለ
ወገነ ሙስሊሙን እያብጠለጠለ
እንደ ቡደን ቃዦች ሌላውን እያለ
በፓርላማው መድረክ ፎከረ ሸለለ

መለስ ቀለስ ብሎ ባያገኝም እቻ
ፈጥሮ ሲያል ወርዷል የራሱን ጉልቻ

ኦክቶበር 20, 2012